Ministry of justice


የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ የካቲት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 17
ADDIS ABABA 11th February, 2011


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፯፻/፪ሺ፫

ለጅጅጋ-ደገሐቡር አካባቢዎች የገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከሳውዲ የልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ......ገጽ ፭ሺ፯፻፴፮


CONTENTS


Proclamation No. 700/2011

Saudi Fund for Development Loan Agreement for Financing the Rural Electrification Project in Jijiga-Degahabur Ratification Proclamation Page 5736


## አዋጅ ቁጥር ፯፻/፪ሺ፫

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሳውዲ የልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለጅጅጋ-ደገሐቡር አካባቢዎች ገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፴፯ ሚሊዮን፭፻ሺ የሳውዲ ሪያል /ሠላሳ ሰባት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ የሳውዲ ሪያል/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሳውዲ የልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፪ ቀን ፪ሺ፲ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ባካሔደው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለጅጅጋ-ደገሐቡር አካባቢዎች የገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከሳውዲ የልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 700/2011.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE SAUDI FUND FOR DEVELOPMENT

**WHEREAS** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Saudi Fund for Development stipulating that the Saudi Fund for Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 37,500,000 Saudi Riyals (thirty seven million five hundred thousand Saudi Riyals) for financing the Rural Electrification Project in Jijiga-Degahabur, was signed in Addis Ababa, on the 2nd day of March 2010;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 11th day of January, 2011;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Saudi Fund for Development Loan Agreement for Financing the Rural Electrification Project in Jijiga-Degahabur Ratification Proclamation No. 700/2011".


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Ministry of justice

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሳውዲ የልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፪ ቀን ፪ሺ፲ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 3/514 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፴፯ሚሊዮን፭፻ሺ የሳውዲ ሪያል /ሠላሳ ሰባት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ የሳውዲ ሪያል/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማ ድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement No. 3/514 signed on the 2nd day of March 2010 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Saudi Fund for Development is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 37,500,000 Saudi Riyals (thirty seven million five hundred thousand Saudi Riyals) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date.</u>**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of February, 2011**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት